መስከረም ፲፰ ቀን ፳፻ ዓ.ም (ሴብቴምበር 2007)

# <u>የፉራ ፖለቲካ !?</u>

ከአያልነሽ

ጨዋታን ጨዋታ ያመጣዋልና በዚህ ሰሞን በውጭው ዓለም በደራው ''ፖለቲካ'' ይሁን ምንነቱ ባልታወቀ ''ግርግር'' መሃል፣ ብዙ ብዙ ነገሮችን በመስማትና በመመልከት አንዳንድ ትዝታዎች ፈንጥቀውብኛል። በተለይማ ''ፉራ'' የሚለውን አባባል ሰስማ ወደ ኋላ ወደ ልጅነቴ ዘመን መልሶኛል። እርግጠኛ ነኝ ''ፉራ'' የሚለው ቃል አማርኛ ይሁን እንጅ በተለምዶ በኢትዮጵያችን ቃሉን ለመጠቀም የማይፈቀድላቸው ሰዎች አሉ ከነኝህም ውስጥ፤ የሃይማኖት አባቶች(ቀሳውስት ዲያቆናት፣ ሸኮች ደረሳዎች ወዘተ፤) የሃይማኖት እናቶች፤ (መነኮሳት መዘምራን ወዘተ) የእድሜ ባለፀጋዎች (አባቶች፣ እናቶች) የፖለቲካ ሰዎች በተለየም በፖለቲካው ዓለም ትልቅ ሚና እንጨወታለን የሚሉና በፖለቲካ ድርጅታቸው ውስጥ (የመሪነት ወይንም የአመራር ቦታ ላይ) የተቀመጡ ወይ ያሉ ሰዎች ወዘተ፤ እንዲሁም በመንግስት ደረጃ የተሰየሙ ወይ (በሥልጣን መንበሩ ላይ የተቀመጡ) ሰዎች ሊጠቀሙባቸው የማይገቡ ቃል (ቃላት) አሉ፤ ብዙ ናቸው ከነዚህ ውስጥ አንዱ ''ፉራ'' የሚለው ነውር አባባል ነው። ይባስ ብሎ ግን''ፓለቲካ'' የሚል ቃል ሲጨመርበት በቃሉ ምክንያት የቃሉን ተጠቃሚ ሰው ወይ ሰዎችን እንድንመርምር ይጋብዛል። ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያለው አንድ አጋጣሚ አስታውሳለሁ። ከላይ እንዳልኩት የጨወታ ነገር ሆነና በጨወታ መሃል ጨዋታን ጨዋታ ያመጣዋል ሆኖብኝ እንጅ ይህንን ጨዋታ እዚህ ልደባልቀው አላሰብኩም ነበር።

ካልተሳሳትኩ ከ6 ዓመት በፊት ከሴብቴምበር 11 በኋላ 2001 ዓ.ም (በፈረንጆች) አቆጣጠር የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ቡሽ ወደ ኢራቅ ጦራቸውን ሊያስገቡ ከጅለው፣ ጉዳዩ በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት መወሰን ነበረበትና የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ነገሩን አኀተተባቸው። ወደ ኢራቅ ጦራቸውን ለማስገባት የቸኮሉት ቡሽ፣ ጦራቸውን የማስገባቱን ጉዳይ በተባባሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር አባል የሆኑት ጀርመንና ፈረንሳይም አጥበቀው ከተቃወሙት ውስጥ ነበሩ። በተለይ ፈረንሳይ ''ድምጽን በድምጽ የመሻር''(ቪቶ ፓወር) ኃይል ካላቸው ውስት አንዷ ነበረችና ይሄንን የቡሽ ፍላጎት አጥብቃ ተቃወመች። በዚህ በጀርመንና በፈረንሳይ አቋም የተናደዱት የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ቡሽ፣ ከሳቸው አገር ጋር እኩልና በአቻ ደረጃ የሚገኙትን እነዚህን የአውሮፓ ሀገራት ''አሮጌ አውሮፓዎች (ኦልድ ዩሮፕ) ብለው ሲያጣጥሉዋቸው፣ በቴሌቭዥን የተመለከቱት አውሮፓውያን ሆኑ በአውሮፓ ውስት የሚኖሩ አሜሪካዊያን፣ በቡሽ ንግግር ከፍተኛ ኃፍረት ተሰምቷቸዋል። በኃብቷና በኃይሏ የምትተማመነውና ለዓለም ዴሞክራሲ አርዓያ ነኝ የምትለው አገር መሪ የሆኑት ፕሬዚዳንት ቡሽ፣ ይሄንን ቃል በማለታቸው አሜሪካውያንን ሊያስገምት የሚችል አባባል ከመሆኑ በላይ ለዓለም በአደባባይ በቴሌቭዥን መረጨቱ ደግሞ ከአውሮፓያኖች የበለጠ አሜሪካዊያኖችን አስቆጭቶና አሳዝኖ እንደነበር ይታወሳል።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

በቅርቡ በአሜሪካ አገር የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ድርጅት መልዕክተኛ አባል የሆኑት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፤ በዋሽንግተን ዲሲ ለተሰበሰበው ህዝብ የመጀመሪያ ንግግር ባደረጉበት ወቅት፤ የሳቸውን "የሠለጠነ ፖለቲካ” ለማስረዳትና ፖለቲካቸውን ለማራመድ፣በሳቸው አባባል በመንገዳቸው ላይ የተሰነቀሩ አሮጌ ፖለቲከኞችን "ፋራ ፖለቲከኞች” በማለት ከመንገዳቸው ገለል እንዲሉላቸው አስጠንቅቀዋል። ዶክተሩ እነኝህን "የፋራ ፖለቲካ” አራማጆችን (በቃል ያሉትን መድገም ስላልፈለግሁ ነው) በመንገዳቸው ላይ ከተገኙ፣ እያፀዱና እየጠረጉ መራመድ እንዳለባቸው አስምረውበታል። ንግግራቸው ባልተቋረጠ ጭብጨባ እየታጀበ መቀጠሉ ደግሞ፣ ለዶክተሩ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚያሳድርባቸው መገመት አያዳግትም። ለመሆኑ አንድ በሕዝብ ተመረጥኩ፣ "የሠለጠነ” ፖለቲካ አራማጅ ነኝ የሚል ሰው "ትህትና” የተባለውን ኢትዮጵያዊ እሴታችንን እንዴት ይዘነጋል? የኢትዮጵያችን ትህትና፣ መከባበርና <u>ሰው ምን ይለኛል</u> የተባለው እሴታችንና፣ ሰዎችን የማክበሩ ትልቁ ባህላችን መገለጫው "ክብርትና ክቡር” መባባሉ ብቻ ነውን? እንዲያው ለነገሩ "ፋራ” ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ቃል በአማርኛችን መዘገበ ቃላት ውስጥ ይገኛል? ካለ አማርኛ መዝገበ ቃላችንስ "ፋራ” የሚለውን ቃል ምን ትርጉም ይሰጠዋል? ለመሆኑ የ"ፋራ” ፖለቲካ ማለት ምን ማለት ነው?

ይህንን ቃል የተጠቀሙት ዶክተር ከመጠቀማቸው በፊት መጀመሪያ አስበውበት ነበር? ምንስ ለማለት ፈልገው ይሆን? ወዘተ...

እርግጠኛነኝ ለማለት ባልደፍርም፣ እኔ እስከማውቀው ድረስ ፋራ የሚባለው ቃል በተራ አባባል (በአራዳ ቋንቋ) ባላገር ለማለት ሲሆን፣ በአራዳው ቋንቋ ፋራ የተባሉት "ባላገሮች” ደግሞ ይሄንን የአራዳ ቋንቋ ተጠቃሚዎችን (ፋራ ባዮችን) "ጨሌዎች” ይሏቸዋል። ሁለቱም ቃላት የያራሳቸው አሉታዊ ትርጉም ሲኖራቸው እነኝህን ቃላት የሚጠቀሙባቸው ሰዎች ደግሞ በቃላት አጠቃቀማቸውና ሰዎቹ በተጠቀሙበት ሁኔታ የሚሰጠው ትርጉምና የፈጠረው ስሜት እንደየሰዎቹ ሁሉ፤ ክብደቱም ይለያያል። በመሆኑም ማንኛችንም ከመናገራችን በፊት መጠንቀቅንና ማስተዋልን የግድ ይለናል። ለዚህም ነው በማስተዋልና በመጠንቀቅ ለሚደረጉ ንግግሮች ኢትዮጵያዊ የሆነው ምሳሌዊ የአነጋገር ዘይቤያችን "ያወቀ ተጠነቀቀ” በማለት ሲገልጸው፣ እንዳመጣና እንዳፈቀደው ለሚናገር ደግሞ "አለዋቂ ሳሚ ...” ይባልና ግምት ውስት ያስገባል።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

ብልጥ ወይም አዋቂ ሰው ከሌሎች ስህተት ይማራል ይባላል። አባባሉ ድንቅ አባባል ነው ለተጠቀመበትና ላወቀበት። መለስ ዜናዊና ድርጅቱ ወያኔ በኢትዮጵያ በትረ ሥልጣኑን በያዙ ማግስት ያበዱበት ወቅት ነበርና መለስ በጣም የተራቀቀና "የሠለጠነ” መሥሎት የኢትዮጵያ ሕዝብ የተዋደቀለትን ሰንደቅ ዓላማ ያነሰ ለማድረግ "ባንዲራ ጨርቅ ነው” በማለት በታሪኩ ላይ በተሳለቀ ጊዜ፣ ከሕዝብ ጥርስ ምን ያህል እንደከተተው የምናስታውሰው ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያ በሰንደቅ ዓላማውና በታሪኩ የተቀለደበት የኢትዮጵያ ሕዝብ 14 ዓመት ሙሉ

እንደአላዋቂና እንደልተከፋ መስሎ ሳያሳይ የሆዱን በሆዱ ይዞ ጊዜ ጠብቆ፣ እድል ሲያገኝ፤ ግንቦት 7 1997 ዓ.ም ለቡድኑና ለመለስ ዜናዊ አይቀጡ ቅጣት በዓለም ፊት ሰጥቶታል። ከዚህም መማር በተገባ ነበር። በተለይ ደግሞ ለሕዝብ ቆመናል፣ ተመርጠናል የሚሉ ሰዎች በተቻለ መጠን እንኳንስ ሕዝብን ያክል ነገር ቀርቶ ማንኛውንም ሰው ትሁት ሆነው መቅረብ ይጠበቅባቸዋል። በተለይ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዚህ በኩል ማታለል አይቻልም ባይ ነኝ።
ከአነጋገር ይፈረዳል ካያያዝ ይቀደዳል ይባላል። የአሁኖቹ የዘመናችን ፖለቲከኞች፣ ፖለቲካችው ምን ያህል የ"ሠለጠነ" እንደሆነ ሲነግሩን፣ ያ "የፋራ" (የባላገር) ፖለቲካ ምንኛ ዕንቅፋት እንደሆነባቸው እየገለጹ ሲያስረዱ፣ እንዲህ ይላሉ "ከ80 ዓመት አሮጌ ወይ ሽማግሌዎች ጋር እንዴት የ50 ዓመት "ወጣቶች" መነጋገር ይችላሉ? እስከማለትም ደፍረዋል። "የሀሳብ እንጅ የሰው ጠላት የለንም" የሚሉት "ወጣቶቹና ሥልጡን ፖለቲከኞቹ" ዋና እንቅፋትና ጠላት የሆኑባቸው ሽማግሌዎችና በእነርሱ አባባል "አሮጌ ፖለቲካ" አራማጆችን፣ ጸረ-ዘመናዊና ጸረ-ሥልጣኔ ብለው ፈርጀዋቸዋል - በዘመናዊው የቅራኔ አፈረጃጀት ማንፌስቷቸው። "የሃሳብ እንጅ የሰው ጠላት የለንም የሚሉት" የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ሰዎች አንዳንዶች፣ በእነርሱ ቤት ከ30 - 50 ዓመት ያሉት የላእላይ ምክር ቤት አባሎች ራሳቸውን ለዓቅመ-ዓዳም ያልደረሱ (አንደር ኤጅ) አርገው እየቆጠሩ ይሆን ሌሎቹን አሮጌዎች የሚሏቸው? "እነኝህ ሥልጡን ፖለቲከኞች" ለ"ሠለጠነው" ፖለቲካቸው ትልቁ ደንቀራ የሆነባቸው ደግሞ፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚገፋው ክፍል ሲሆን፣ በነርሱ "በሠለጠኑት ፖለቲከኞች" አባባል/ቋንቋ "ኢትዮጵያዊ አክራሪነት"(ሀርድ ላይነር) በማለት ይግልጿቸዋል ። እኔው ራሴ ደግሞ እንዳጋጣሚ በዚሁ "የፋራ ፖለቲካ ውስጥ" አድጌ የኖርኩበት ነውና ባላገርነቱ እየገረገረኝ እንዳልሠለጥን አድርጎኛል። እንደኔ እንደኔ ከሆነ አሁንም ይህንን የ"ፋራ ፖለቲካ" አልጠላሁትም፤ እሱም ቢሆን አለቀቀኝም። ባላገር ነኝና አክርሬ ይዠዋለሁ። የማቱሳላን ዕድሜ ይስጠኝ እንጅ በዚህ ጉዳይስ የምሠለጥን አልመሰለኝም፤ አዝናለሁ። ድንገት ይህ የኢትዮጵያዊነት "አክራሪነት" እድገቴ የሚያስከፋው ሰው ካለ ከወዲሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ምን ይደረግ የባላገር ነገር ሥልጣኔ ቶሎ አይገባን!

በኢትዮጵያችን (83%) ከመቶው 83 እጅ በገጠሩ የሚኖረው ህዝብ ባላገሩ ነው። የሀገራችን ኢኮኖሚ መሰረቱም ግብርና በመሆኑ ይኸው 83% የሚሆነው ህዝባችን ደግሞ የገጠሩ ነዋሪ መሆኑ ግልጽ ነው። ዛሬ ቅንጅትና ህበረትን ድምፁን በመስጠት አቸናፊ ሆነው እንዲወጡ ያደረጋቸው፣ የነኝህን "ሠለጠንን" የሚሉትን ዘመነኛ ፖለቲከኞች ማንፌስቶን አንብቦ ሳይሆን፣ መለስ ዜናዊና ድርጅቱ ወያኔ ያጣጣሉበት ሰንደቅ ዓላማዉና፣ የተሳለቁበት ኢትዮጵያዊው የጀግንነት ታሪኩ ቁጭት፣ መሰረት ሆኖት ነው። እንደውነቱ ከሆነ ይህ ባለገር ሕዝብ፣ ዛሬ ለእነኝህ የፖለቲካ ድርጅቶች ድምጹን ሰጥቶ እንዲያሸነፉ ሲያደርግ ለ14 ዓመት የወያኔ አገዛዝ ባደረሰበት ግፍ ተነሳስቶ ዓይኑን ጨፍኖ ከወያኔ አገዛዝ መገላገሉን በመመኘት ነበር እንጅ፣ ዛሬ የዘመናችን ፖለቲከኞች እንደሚነገሩን "የሠለጠነው ፖለቲካና የፋራው ፖለቲካ" ምንትስ የሚሉት፣ ገብቶትና ተረድቶትም አይደለም። ይህንን "የሠለጠነና የፋራ ፖለቲካ" የሚባለውን ቲዎሪ (ንድፈ-ሃሳብ) ዛሬ እኛ እንዲገባን በፈረንጆች አገር አውሮፓና

አሜሪካ ለምንኖር ባላገሮች እየዞራችሁ በነጻነት እንደምትነግሩን ሁሉ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመረጣችሁ፣ ድምፁን ለሰጣችሁና ለሞተላችሁ ሕዝብ፣ ድምፁን አስመልሱለትና በነጻነት እንደኛ ሃሳቡን ከእናንተ ጋር እንዲለዋወጥና እንዲረዳው ልታደርጉት ይገባል። እንዲያው ለነገሩ ''የፉራ ፖለቲካ'' ያሉት ዶክተር ድርጅታቸው የሆነውን ቅንጅትን የመረጠው ባላገሩ ህዝብ ለመሆኑ ልብ ብለዋል?

በዶክተሩ ግንዛቤ ''የፉራ ፖለቲካ'' ሲሉ ምን ማለት ይሆን? እንዲህ እንዲህ ዓይነት ቃሎችን ሊጠቀሙ የማይፈቀድላችው ሰዎች ሲሉ(ሲናገሩ) ብንሰማ፣ እኛ ባላገሮች፣ እረ በኢትዮጵያ ዓምላክ! ነውር ነው እንዲህ አይባልም ብንል፣ ለሚቀጥለው ''ምርጫ'' የምርጫ ካርድ ልንከለከል ነው? እርግጥ ነው ባላገር አይናገርም - ካልባሰው በቀር፤ ግን ብሶት ሲናገር ደግሞ ብሶቱን ለማዳመጥ አለመሻት ምንን ያመላክታል? መማሩና መሠልጠኑስ ምኑ ላይ ነው? በሕዝብ ተመረጥን ማለቱስ። እረ! እየተስተዋለ እባካችሁ ''ክቡራንና ክብርቶች''!

ለነገሬ መቋጨ ትሆነኝ ዘንድ ይህችን የግጥም ስንኝ ተውሻለሁና እነሆ!

ተንበርክኮ ፀሎት ተንጥፎ ልመና፣
ለአምላክ ከሆነ እንጂ ለሰውማ አይሰራ፣
ጎንበስ ያሉለት ሰው ልመና የበዛበት፣
መርገጥ መቅበር እንጂ፣ ማዘን አይመጣለት።

ምንጭ፥ ከሀማ ቱማ (ሐበሸኛ) ከሚለው የግጥም ጥራዙ ውስጥ የተወሰደ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ ሀማ ቱማ አመስግናለሁ!

በመጨረሻም፥ ''እርስዎም ይሞክሩ'' የጥያቄና መልስ ግብዣዬ ላይ ተጋብዘዋልና እባክዎ! ጌታዬ/እመቤቴ ለጥያቄዬ መልስ የሚሆን ካገኙ ይሳተፉ/ተሳተፉ ለተሳትፏችሁ አመስግናለሁ። ጥያቄዎቹ እነሆ!

- በአሜሪካ እየዞሩ ያሉት የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የመልዕክተኞች (ኢንጅነር ኃይሉን ያልጨመረው ) ቡድን ቃል አቀባይ የሆኑት ዶክተር፣ እድሜያቸው ስንት ነው?
- በአሜሪካ እየዞሩ ካሉት የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የመልክተኞች ቡድን አሁንም (ኢንጅነር ኃይሉን ያልጨመረው) የድርጅት ክፍል ተጠሪ የሆኑት ኢንጅነርስ እድሜያቸው ስንት ይሆን?
- እንዲሁም በአውሮፓ የተንቀሳቀሰው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የመልክተኞች ቡድን አባል አንዱ የሆኑት ዶክትር እድሜያቸው ስንት ነው?
- የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ መሥራቾች ውስጥ አንዱ የሆኑት ፕሮፌሰርስ? እድሜያቸው ስንት ይሆን? ሌሎችስ አመስግናለሁ

የሕዝብ ድምጽ ይከበር!
የታሰሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ቸር ይግጠመን